በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




# ከኦክቶበር 1-10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከኦክቶበር 11-20/2026 እና ከኦክቶበር 21-31/2026

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ31 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 30.1-119 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መንደር11 119፣ ድሬ ሸከናሁሲን 85.5፣ ጊኒር 54፣ ጎዴ 40.4፣ እርምጭ 39.2፣ ቅዳሜ ገበያ 38.6፣ አርባምንጭ 32.2፣ ማጂ 31.2፣ ዲመካ 31፣ ዶሎ ኦዶ 30.2፣ ዶሎመና 30.1 ይገኙበታል፡፡




ምስል1: ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ጥቂት የአርሲና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜንና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኙዋክ፣ ኑዌር እና መዠንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል ፋፈን፣ ጃረር፣ ኤረር፣ዶሎ፣ ቆራሄ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ ላይ ከ15-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ የአርሲና ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜንና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኙዋክ፣ ኑዌር እና መዠንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል ፋፈን፣ ጃረር፣ ዶሎ፣ ቆራሄ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ በአብዛኛ መደበኛ እና ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብ አጋማሽ እና በሰሜን መዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በማበብ እና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ላሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለሌሎች የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም በወቅቱ መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነበረ። እንዲሁም በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ቆላማው አካባቢ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በቂ የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጀመርያው አስር ቀናት በአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ኦጋዴን ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ መካከለኛ ተከዜ፣ እንዲሁም በጥቂት መካከለኛና ታችኛው አባይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ነበራቸው፡፡ በመሆኑም ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ገብዓት ጥሩ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ይህ ሁኔታ በተለይም ዋነኛ ወቅታችው ለሆኑት ለአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን ለመካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነበር (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፣ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው።በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ያገኛሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መከከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በሌላ በኩል ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር11-20/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

**ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን**

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች አብዛኞቹ የሸዋ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የአዊ፣ ምዕራብ ጎጃም እና ባህርዳር ዙሪያ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ፣ የኑዌር እና መዥንግ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል እና ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ ደቡባዊ ስፍራዎች፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| አፋር | በጥቂት የክልሉ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 2/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንድሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

## 2.4 እ.አ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የበጋ ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን የሚደርስ የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ-ተኮር የውሃ-ሜቲዎሮሎጂ ምክረ-ሀሳቦች ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር አምራች ዞኖች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም ፣ ባህርዳር ዙሪያ ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ ፣ ኑዌር፣ መዥንግ ፣ ካማሺ፣ መተከል ፣ ማኦ ኮሞ ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ ምዕራብ ኦሞ ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መኖር እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ | ➢ በአንዳንድ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በሰብሎች ላይ መተኛት<br>➢ የአረም መከሰት<br>➢ እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ የድጋሚ አረምን ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር<br>➢ እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን በጊዜ መዝራት |

## በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች

| ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም ፣ ባህርዳር ዙሪያ ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ ፣ ኑዌር፣ መዥንግ ፣ ካማሺ፣ መተከል ፣ ማኦ ኮሞ ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ ምዕራብ ኦሞ ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መኖር እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>➢ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>➢ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ለቋሚ ተክሎች እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ | ➢የአረም መከሰት እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢በአንዳንድ አካባቢዎች ቀድመዉ የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ<br>➢የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ የድጋሚ አረምን ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር<br>➢ እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን በጊዜ መዝራት |

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦጋዴን፣ በላይኛውና መካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በታችኛው አባይ | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ በመጠን መሻሻል | • የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የሚገኘውን የዝናብ ውሀ በአግባቡ መጠቀም<br>• ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • በላይኛውና መካከለኛ ዋቤ ሸበሌ፣ ታችኛው ተከዜና በጥቂት በላይኛው አዋሽ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ<br>• መጠነኛ የውሃ ፍሰት ሻሻል | • ከፍተኛ ትነት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • ወራጅ የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውሃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የአየር ሁኔታ መረጃዎችን በቅርበት መከታተል |
| **ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • በአብዛኛው አፋር፣ አዋሽ፣ ደናክል፣ መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ አዋሽ፣ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | • ከፍተኛ ትነት | • የውኃ እጥረት በሚገጥማቸው አካባቦዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር<br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et